ጥር 20 ቀን 2005 ዓ.ም

ግልፅ ደብዳቤ ለጀርመን የአማርኛ አገልግሎት ክፍል

ቦን

ይህን ደብዳቤ ለመፃፍ ያሳሰበን ምክንያት ትናንት ጥር 19 ቀን 2005 ዓም በእለተ ሰንበት ስለ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ችግር የተደረገዉን ዉይይት በመስማታችን ነዉ።
በእኛ እይታና ግንዛቤ ይህ ዉይይት አይደለም።
ለምን ቢባል የችግሩ መንስኤ በሚገባ ሳይገለፅ ዉይይቱ ስለ አባቶች በዉጭና በኣገር ቤት መከፋፈል፤ ተጀምሮ ስለነበረዉ የእርቅ ድርድር አለመሳካት፤ ወዘተረፈ ብዙ ተባለ። ዉይይቱን የመራችዉ ጋዜጠኛና ተዋዋዮቹም ከአንዱ በስተቀር ወንጌል ሰባኪ ስነ ምግባር አነብናቢ ፈሪሳዉያን ሆነዉብናል።
አስገራሚዉ ነገር በምድረ ኢትዮጵያ በቤተ ክርስቲያኑ ሆነ በቤተ መስጊዱ ዉስጥ ጣልቃ ገብቶ ምእመናን የሚያምሰዉ፤ የሚያስረዉ፤ የሚገድለዉ፤ የሚያሰድደዉ ትልቅ ቀንዳማ ሰይጣን መንግስት ተብዬዉ እራሱን የትግሬ ህዝብ ነፃ አዉጭ ግንባር (ህወሀት) የሚለዉ ቅጥረኛ ቡድን ነዉ።

ወታደራዊ ደርግ አገር አጥፍቶ፤ ጥርጊያ መንገዱን ለወያኔና ሻእቢያ አመቻችቶ በግንቦት ወር 1983 አ.ም ሲንኮታኮት የታሪክ ጠላቶቻችን እቅድና ዝግጅት ተሳክቶ በትዉልድ ኢትዮጵያዊ በሆኑ ወገኖች ተግባራዊ እንዲሆን የእቅዱ ማስፈፀሚያ ስልት የኢትዮጵያን ህዝብ በጎሳ ከፋፍሎ ርስበርስ በማጋጨት የኢትዮጵያዊነትን ሀገራዊ ስሜትና ኩራት አሶግዶ እትዮጵያን ከአለም ካርታ ላይ ለመፋቅ ታስቦ የባንቱስታን የጎሳ ፖለቲካ በምእራባዉያን የፖለቲካና ኢኮኖሚያዊ ርዳታና ድጋፍ ተግባራዊ ከሆነ ጀምሮ በሁሉም አካባቢ በጎሳ ማፅዳት ዘመቻ የወደመዉ ሃብትና ንብረት፤ የጠፋዉ ህይወት ከፍ ያለ ነዉ።
የወያኔዉ መሪ አቶ መለሰ ያሜሪካንና የእንግሊዝ መንግስታትን ይሁንታና ፈቃድ ከአገኘ በሁዋላ ቤተ መንግስቱን ብቻም ሳይሆን ቤተ ክህነቱንም መቆጣጠር ሰለፈለገ ፓትርያርኩን ብፁእ አቡነ መርቆሪዎስን በጠመንዣ አፈሙዝ አስገድዶ ከመንበራቸዉ በማስወገድ የራሱን ካድሬ አባ ገብረ መድህንን አባ ዳዉሎስ ብሎ አሾመ። በዚህም ሁኔታ ህገ ቤተ ክርቲያን ተፋለሰ። በአንድ ኣገር አንድ ፓትርያርክ በህይወት እያለ ሌላ ፓትርያርክ መሾም ክክል ነዉ።

በአባ ዳዉሎስ እንበለ ሕግ መሾም ምክንያት ታላቅ ቀዉስ ተከተለ። በጎንደር አደባባይ ኢየሱስ፤ በአክሱም፤ በአዲስ አበባና ሌሎች ኣድባራት ከፍተኛ ተቃዉሞ ተነስቶ በወያኔ ወታደራዊ ርምጃ የደረሰዉ ሰቆቃና ግፍ አይዘነጋም። በአዲስ አበባ እስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲን ሰማእት የሆኑት አባ ፈቃደ ስላሴን አንረሳቸዉም።

*የአባ ፓዉሎስን ምግባረብሉሹነት በመቃወማቸዉ ምክንያት አይደለ.ም እንዴ ብዙ አባቶች በወያኔ አፋኝ ልዩ ፖሊስ የተደበደቡት?*

*ብፁእ አባታችን አቡነ መርቆሪዎስ ከተጋዙበት የእንጦጦ መቃብር ቤት አምልጠዉ ወደ ኬኒያ በመሄድ ቀጥሎም ወደ ሰሜን አሜሪካ በመዝለቅ በእግዚአብሄር ቸርነት ተግባራቸዉን በመፈፀም ላይ ይገኛሉ። ሰሞኑን በአለ ጥምቀት አስመልክቶ በሰጡን ቃለ ቡራኬ እጅግ በጣም ተደስተናል። ወያኔዎች በዉጭ ያለዉንም ሕዝብ ገንዘቡን ብቻም ሳይሆን መፈሳዊ ኑሮዉንም ለመቆጣጠር ይንጠራራሉ። በዚህም ረገድ የዉጭዉ ሕጋዊ ሲኖዶስና አቢያተ ክርስቲያናት መጠናከርና መፋፋት ለወያኔ ዘረኞች ታላቅ መጋኛ ሆኖባቸዉ ይቅነዘነዛሉ።*

*ሁለቱ ዋና የወያኔ መሪዎች በአለፈዉ ዓመት ነሐሴ ወር ተቀሰፉ። በአዲስ አበባ ከታየዉ ትርኢት በጣም ያስገረመን ፀረ ሸዋዉ፤ ፀረ አማራዉና ፀረ ኢትዮጵያ የነበረዉ፤ በአንድ በኩል ኮምኒስት ነኝ የአልባኒያዉ መሪ ተከታይ ነኝ፤ በሌላ በኩል ደግሞ በሲአይኤዉ አባወራ ፓዉል ሄንዝ አቅራቢነት ለአሜሪካን የቡሽ አስተዳደር ለአፍሪቃ ቀንድና የቀይ ባሕር ቁልፍ አካባቢ ጥቅም አስከባሪነት ታማኝ ተላላኪ የነበረዉ ግለሰብ በሸዋ ምድር በቅድስት ሥላሴ ያርበኞች መካነ መቃብር ሲቀበር መታየቱ ነዉ።*
*ከቀብሩ መልስ ያቶ ኃይለ ማርያም ደሳለኝን ሹመት አስመልክቶ የወያኔዉ ዋና የርእዮት ሃላፊ አቦይ ስብሃት ነጋ ባቶ መለሰ ዜናዊ ባለቤት ወይዘሮ አዜብ መስፍን እንደ አሮጌ ዉሻ ወለበል ተብሎ በሱካር ኬሻ ቁልል ዉስጥ ተወሽቆ ከቆየበት ብቅ ብሎ "የአማራ ሕዝብንና የኦርቶዶክን ሰብረናል" በማለት ቅርሻቱን ሲተፉ ነበር። ምን ይህ ብቻ ሰሞኑን በአዲስ አበባ ያሉት አባቶች በአደረጉት ሰብሰባ አቶ ስብሃት በአካል ተገኝቶ "አባ መርቆሪዎስ ይመለሱ ከምትሉ ለምን መንግስቱ ኃይለማርያም ይመለስ አትሉም " እያለ እንዳስፈራራቸዉ ከተለያዩ ድረ ገፆች አንብበናል። በተጨማሪም አባ መርቆሪዎስ የሚመለሱ ከሆነ የራሳችንን የትግሬ ፓትርያርክ አክሱም ላይ እሾማለን መባሉ ተሰምቶዋል። ለዚህ ተገቢ መልስ መስጠት ያስፈጋል።*
*ለመሆኑ አክሱም የማን ናት? አክሱም የኛ ቅድስት ሀገር ናት።*
*አክሱማዉያን ጥንት፤ ዛሬም ምንምጊዜ ፍፁም ኢትዮጵያዉያን እንጂ ወያኔዎች አይደሉም።*
*አክሱሞች ቤተ ተክለ ሃይማኖት ናቸዉ። ወያኔዎች በደደቢት በረሃ የጎጥ ፓትርያርክ ለመሾም ይችላሉ። አክሱም ግን ዝር አይሉም። ያክሱም አባቶች እኮ ናቸዉ የአባ ጳዉሎስን ሹመት በመጀመሪያ ደረጃ የተቃወሙት። ስለ ቅድስት ሀገር አክሱም ያጤ ዘርአ ያእቆብ ዜና መዋእል የሚለዉን እንጥቀስ፤*
*ወዘንተ ኩሎ ዘሰርአ ገብረ መስቀል ንጉሰ ርቱአነ ሃይማኖት ወህደሰ ንጉሰነ ዘርአ ያእቆብ ወሪዶ ሀገረ አክሱም ርእሰ አህጉር ወትምክህተ ኩሉ አለም ወትርሲቶሙ ለነገስት።*
*ርቱእ ሃይማኖተኛዉ አጤ ገብረ መስቀል የሰራዉን ሁሉ ንጉሰ ዘርአ ያእቆብ ያገራት ዋና፤ የአለም መመኪያና ለነገስታ እንቁ በሆነችዉ አክሱም ወርዶ አደሰ።*

በዉጭ የሚገኘዉ ሲኖዶስ ያወጣው መግለጫ ትክክል ነዉ። ከእንግዲህ ወዲያ እርቅ እያሉ ጊዜ ማጥፋት ፋይዳቢስ ነዉ። በዉሳኔዉ መሰረት ጠንክሮ መስራት ነዉ። በአባቶች መካከል ምንም መለያየት የለም። ቤተ ክርስቲያን አንዲት ናት። በስልጣን ለመቆየት ሲል ህዝብንና ቤተ ክርስቲያንን በዘር በጎሳ የሚከፋፍል ወያኔ ነዉ። ለሃይማኖተ አበዉ ቀናኢ የሆነዉ ወገን ተባብሮ ይነሳ። ሰበብ አስባብ እየፈለጉ ፀጉር መሰንጠቅ፤ ፀረ ወያኔ ትግሉን ማዘናጋት፤ ማደናቀፍ ገለልተኛ ነኝ እያሉ ማወናበድ ከአፍቃሪ ወያኔነት ሌላ ምን ሊባል ነዉ? በሁለት ቢላዎ መብላት ይቁም። ወያኔ ወዶ ሳይሆን ተገዶ መወገድ አለበት። የወያኔን ዘረኛ እብጠት ይንተራፋል። የኢትዮጵያ ህዝብ ነፃና ዲሞክራሲያዊ ስርአት በወያኔ መቃብር ላይ ይመሰርታል። ይህ ሲሆን ብቻ ነዉ ህጋዊ ሲኖዶስ ወደ አገር ቤት የሚመለሰዉ።

በተረፈ የቅቤ እንጎቻ ጋጋሪዎችና የቀበሮ ባህታዉያነን ሰለኦርቶዶክስ ሃይማኖት መከፋፈል አያሳችሁ አታሳዝኑ።

የጀርመን ድምፅ ጋዜጠኖች መሞዳሞድና መሸፋፈጥን አቁሙ። የወያኔ በሃይማኖት ጣልቃ ገብነት ለምን ስዉር ምሲጢር ሆነባችሁ? መንስኤዉን ሸፋፍናችሁ ምነዉ ሰለ አባቶች መከፋፈልና እርቅ ነገር መክሸፍ ያዞ አንባ ታለቅሳላችሁ? የቀረዉ ቢቀር እንኩዋ ከቡር ሻለቃ ግርማ ው-ልደ ጊዎርጊስ የወያኔዉ መንግስት ፕሬዘዳነት ከአገር ሽማግሌዎች ጋራ መክረዉ ዘክረዉ ለብፁእ አቡነ መርቆሪዎስ የፃፉትን ደብዳቤ በአሜሪካ ድምፅ ራዲዮ ቃለ መጠይቅ እንዳረጋገጡትና ወዲያዉኑ በመንግስት ጫና እንዲሰቡ መደረጉን እንኩዋን ያለመጥቀሳችሁ በጣም ያስተዛዝባል።

ፃኡ ንኡሰ ክርቲያን !

ኢትዮጵያ በልጆቹዋ መሰዋትነት ለዘለአለም ትኖራለች!!

| | | |
|---|---|---|
| ወይዘሮ ዘብይደሩ ደመቀ | ሽፈራዉ ገዝሙ (አባ ክፋይ) | ጉዳ ቀጀሳ(አባ መሳ) |
| ዶ/ር ገብሬ ጉልቱ | እጥፍ ወርቅ ባልቻ | ዘዉዱ በቀለ |
| ተለአለ ማንበግሮ (አባ ቀብራሬ) | ሰይፉ ሳህሌ | ሳቀች በሳይነህ |